



# ስለ አዲስ ለመጡት ልጆች እንክብካቤ (CARE FOR NEWCOMER CHILDREN – CNC) ሁሉ

*እንኳን ደህና መጡ! የእኛ CNC መርሃ ግብር በተለይ የተነደፈው ለካናዳ አዲስ ለሆኑ ልጆችን ለመደገፍ እና የእነርሱን ቤተሰቦች IRCC የድጋፍ አገልግሎቶች እያገኙ እያለ ነው። እዚህ ያለነው ለማገዝ ነው።*

*ይህ ለእርስዎ እና ለቤተሰብዎ ከፍተኛ ለውጥ የሚደረግበት ወቅት እንደሆነ እናውቃለን። ግባችን ልጅዎ በካናዳ ቤተሰቦችዎ ውስጥ ሲኖሩ እድገታቸውን በመደገፍ እና የልጆቻቸውን በራስ የመተማመን ስሜት በመገንባት ሰላም፣ በራስ መተማመን እና የደህንነት ስሜት እንዲሰማቸው ማድረግ ነው።*

**ልጆች በ CNC መርሃግብር ውስጥ ሲሆኑ ወላጆች ሁል ጊዜ በሁሉም ጊዜ በቦታው ሊቆዩ ይገባል።**

## ከልጅዎ ደህንነት የበለጠ አስፈላጊ የሚሆን ነገር የለም!

ሰራተኞቻችን ብቃት ያላቸው እና ልምድ ያላቸው መሆኑን እርግጠኛ መሆን ይችላሉ።

- ሁሉም ሰራተኞች የጀርባ/የወንጀል ሪኮርዶች ፍተሻዎች እና የመጀመሪያ እርዳታ ስልጠና አላቸው።
- የ CNC መስፈርቶችን እንከተላለን እንዲሁም የጤና እና የደህንነት መመዘኛዎችን ማሟላታችንን ለማረጋገጥ ክትትል ይደረግበናል።
- ሁሉም ልጆች በእኩልነት እና በክብር መያዛቸውን ለማረጋገጥ የጠባይ አስተዳደር ፖሊሲ አለን። ሰራተኞች መልካም ባህሪን ማጠናከር አለባቸው። በልጆች ላይ አካላዊ ቅጣት ወይም በሃይለ ቃል ማነጋገር አይፈቀድም፣ ችላ ማለትም ሆነ ቁጥጥር ማነስ እንዲሁ።
- ሰራተኞች አግባብ ላላቸው ባለስልጣናት ጉዳት የደረሰባቸው ወይም ችላ መባል የተከሰተበትን ልጅ ማንኛውም ሁኔታ ሪፖርት የማድረግ ሙያዊ እና ህጋዊ ግዴታ አለባቸው።

የበለጠ ለማወቅ ፍላጎት ካለዎት የእኛን የባህሪ አስተዳደር ፖሊሲ ወይም የተጠረጠር የልጅ መንሳቀል/ችላ መባል ፖሊሲ ቅጅ ለመጠየቅ ነጻነት ይሰማዎት።

## ከ CNC ምን መጠበቅ ይችላሉ?

በካናዳ በቡድን በቡድን መልክ ለህጻናት የምንሰጠው እንክብካቤ ከሀገርዎ ሊለያይ ይችላል። ስለ ስነስርዓት፣ ምግብ፣ ቋንቋ፣ ትምህርት ወይም የተለመዱ ጉዳዮች ጥያቄዎች ካሉዎት እባክዎ ይጠይቁ። ጥናቶች እንደሚያሳዩት ልጆች በጨዋታ ይማራሉ፣ ስለዚህ ሰራተኞች ትምህርትን፣ በመጫወት ላይ የተመሰረቱ የመማሪያ እንቅስቃሴዎችን ለልጆች ፍላጎቶች፣ እድሜዎች፣ ችሎታዎች እና ባህሎች የሚስማሙ ያቅዳሉ። ልጅዎ ከሌሎች ልጆች ጋር በመግባባት ይለማመዳል እና ለትምህርት ቤት የሚያዘጋጃቸውን ክህሎቶች ያዳብራሉ።

### ልጅዎ ከ CNC ጋር እንዲላመድ እንዴት ማገዝ ይችላሉ?

ልጅዎ CNC ስለ መጀመር ፍርሀት መኖሩ የተለመደ ነው። ሽግግርን ቀላል ለማድረግ ሰራተኞች ከእርስዎ ጋር አብሮ ይሰራሉ፣ ነገር ግን በመጀመሪያ ልጅዎ ሊያለቅስ፣ ሊጣበቅበዎ፣ ወይም ሌሎች ባህሪዎችን ሊያሳይ ይችላል። የልጅዎን ስጋቶች ለማቃለል እንዴት ማገዝ እንደሚችሉ ለተጠቆሙት ሀሳቦች፣ *እንኳን ወደ CNC በደህና መጡ፡- ቀስ በቀስ መለያየቶች የወላጆች መመሪያ ቅጅ ይጠይቁ።*

## በወላጆች እና በሰራተኞች መካከል መግባባት ጠቃሚ ነው!

የ CNC ሰራተኞቻችንን እንድታውቁ እና ስለ ልጅዎ መረጃ እንዲያጋሩ እናበረታታዎታለን። እኛ ሁላችንም አብረን ስንሠራ ልጅዎን መርዳት እና ደህንነታቸውን በተሻለ መንገድ መጠበቅ እንችላለን።


*Funded by: Immigration, Refugees and Citizenship Canada / Financé par : Immigration, Réfugiés et Citoyenneté Canada*

# ስለ አዲስ ለመጡት ልጆች እንክብካቤ (CARE FOR NEWCOMER CHILDREN – CNC) ሁሉ

### ለሠራተኞቹ እነዚህን ስለመናገርዎ እርግጠኛ ይሁኑ፡-

- አለርጂዎች ወይም የምግብ ገደቦች፤
- ሕመሞች ወይም ልጅዎ የሚወስዷቸው መድሃኒቶች (እባክዎን ልብ ይበሉ፡- መድሃኒት የሚሰጠው ለህይወት አስጊ ሁኔታዎች ላይ ብቻ ነው እና ከልጅዎ ወይም ቦርሳዎቻቸው ጋር ፈጽሞ መተው የለበትም)፤
- እና ልዩ ፍላጎቶች ወይም ተግዳሮቶች። ሊረዱዎት ይችሉ ይሆናል!

### ለሠራተኞች እነዚህን መናገር ጠቃሚ ሊሆን ይችላል፡-

- የልጅዎ የእንቅልፍ ወይም የመመገቢያ የጊዜ ሰሌዳ፣
- የልጅዎ ፍላጎቶች እና ተወዳጅ ምግቦች፣
- ከልጅዎ ጋር ሰራተኞች እንዲነጋገሩ የሚረዱ ቃላት፣
- ስለቤተሰብ እና እህቶች እና ወንድሞች መረጃ (ወይም የቤተሰብ ፎቶ ያምጡ)፣
- እና ለልጅዎ የሚንከባከቡበት ልዩ መንገዶች እና ከ CNC የሚፈልጉትን ነገር።

### ሌሎች ሊያስታውሷቸው የሚገቡ ነገሮች፡-

- ለልጅዎ ደህንነት፣ ለአገልግሎቶች የተመዘገበ ወላጅ ብቻ የራሳቸውን ልጆች ማምጣት እና መውሰድ ይችላሉ።
- ልጅዎን ሁልጊዜ ማስገባት እና ማስወጣት አለብዎት።
- በአየር ሁኔታም ሆነ በመርሃ ግብሩ ላይ ለሚሰሯቸው እንቅስቃሴዎችች ልጅዎን በአግባቡ ያልብሱ። ልጅዎ ምን መልበስ እንዳለበት ጥያቄ ካለዎት ሰራተኞችን ይጠይቁ
- የእነርሱን ተደጋጋሚ ተግባራት ለማስጠበቅ እና ልጅዎን ለትምህርት ቤት ለማዘጋጀት በየቀኑ ልጅዎን ማምጣት በጣም አስፈላጊ ነው።ልጅዎ መቅረት ካለበት ለሰራተኞቹ ያሳውቁ።
- ልጅዎ ከታመመ፣ ህመሙ እንዳይዛመት ለመከላከል ቤትዎ ያቆዩት። ትኩሳት ወይም ተቅማጥ ያለባቸው ልጆች ወደ CNC ከመመለሳቸው በፊት ለ 24 ሰዓታት ያህል ከምልክት ነጻ ሊሆን ይገባል።

## ስለ የእኛ CNC መርሃ ግብር ሁሉ

**የተንከባካቢ ስሞች፡-** ______________________________
Caregiver's Name / Nom du dispensateur de soins

**CNC ሰዓታት፡-** ______________________________
CNC Hours / Heures de garde d'enfant

| | አዎ<br>Yes / Oui | አይደለም<br>Non / Non |
|---|---|---|
| **ክትባት ያስፈልጋል**<br>Immunization required / L'enfant doit avoir été vacciné | ○ | ○ |
| **መክሰስ እናቀርባለን**<br>We provide snacks / Nous fournissons des collations | ○ | ○ |
| **ለልጅዎ ምሳ / መክሰስ ምግብ ይዘው ይምጡ**<br>Bring food for your child's lunch/snack / Apportez le déjeuner/la collation de votre enfant | ○ | ○ |
| **በምሳ ጊዜ ልጅዎን ይንከባከቡ**<br>You care for your child at lunch / Vous prenez soin de votre enfant au déjeuner | ○ | ○ |
| **የእንቅልፍ ጊዜ አለን**<br>We have a naptime / Notre programme prévoit une sieste | ○ | ○ |

| | አዎ<br>Yes / Oui | አይደለም<br>Non / Non |
|---|---|---|
| **የሚያዝናና የህጻናት መጫወቻ ያምጡ**<br>Bring a comfort toy / Apportez un jouet réconfortant | ○ | ○ |
| **ተጨማሪ ልብሶችን ያምጡ**<br>Bring extra clothes / Apportez des vêtements supplémentaires | ○ | ○ |
| **የቤት ውስጥ ጫማዎችን ያምጡ**<br>Bring indoor shoes / Apporter des chaussures d'intérieur | ○ | ○ |
| **ብርድ ልብስ ያምጡ (አስፈላጊ ከሆነ)**<br>Bring a blanket (if needed) / Apportez une couverture (si nécessaire) | ○ | ○ |
| **የንጽህና መጠበቂያ እሽጎች ወይም ዳይፐር ያምጡ (አስፈላጊ ከሆነ)**<br>Bring diapers (if needed) / Apportez des couches (si nécessaire) | ○ | ○ |

CMAS
ወጣት ፍልሰተኛ ህጻናት እንክብካቤ እና ስፈራ መደገፍ

ለበለጠ ወላጅ መርጃዎች ይጎብኙ፡-
www.cmascanada.ca

Care for Newcomer Children


*Funded by: Immigration, Refugees and Citizenship Canada / Financé par : Immigration, Réfugiés et Citoyenneté Canada*